የፈተና ዕቅድ አዘገጃጀት

Planning for the test /test blue/

demissie99@gmail.com

27.9.2014

At HKPS

ማለት የፈተና ጥየቄዎች ከመዘጋጀታቸው በፊት ታሳቢ ሊሆኑ የሚገቡ ቅድመ ፈተና ዝግጅቶችን ተጨባጭና ግልፅ በሆነ መልክ የማቀድ ዘዴ ነው።

ተማሪዎች የተማሩትን የትምህርት ይዘት ሽፋን ምን ያህል እንደሆነ

መምህራን ለማስተማር ያዋሉት የክፍለ ጊዜ መጠን ምን ያህል ነው

በትምህርቱ አማካኝነት ተግባራዊ የተደረጉ አጠቃላይና ዝርዝር የትምህርት ዓላማዎች መጠንና ዓይነት ምን እንደሚመስል

እነዚህና መሰል ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ተጠናቀው ሳይዘጋጁ የፈተና ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ተገቢ አለመሆኑ የስነ-ትምህርትና ምዘና ምሁራን አጥብቀው ይገልፃሉ

የፈተና ዕቅድ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች (ተግባራት)

- የትምህርቱ አጠቃላይ ዓላማዎችና ዝርዝር ዓላማዎች ማዘጋጀት
- የትምህርቱ ዋና ዋና ይዘቶችንና ንዑሳን የትምህርት ርዕሶች ማዘጋጀት
- በምዘናው ለመሸፈን የሚፈለገው የትምህርት ይዘት መወሰን
- ለማስተማር የፈጀው የክፍለ ጊዜ መጠን ከዋናና ከንዑሳን ርዕሶች አንፃር ተንትኖ ማዘጋጀት
- በፈተናው ለመመዘን የተፈለገው የተማሪዎች የባህሪ ለውጥ አይነት ምን ምን እንደሆነ መወሰን (ለምሳሌ ለመመዘን የተፈለገው የተማሪዎችን ዕውቀት ግንዛቤ ክህሎት ዝንባሌ የመናገር ችሎታ በምልከታ የሚመዘኑየመስራት ችሎታ ወዘተ ሊሆን ይችላል
- መመዘን ለተፈለገው ባህሪ የሚስማሙ የፈተና ዓነቶች አስቀድሞ መምረጥና መወሰን (ለምሳሌ እውነት ሀሰት አዛምድ ባዶ ቦታ ሙላ የምርጫ የጥያቄ ደረቅ ጥያቄ የተግባር ፈተና ጥያቄዎችን ወዘተ ሊሆን ይችላል በፈተናው ለመመዘን የተፈለገው የተማሪዎች የባህሪ ለውጥ አይነት ምን ምን

የፈተና ዕቅድ ለማዘጋጀት የሚያፈልጉ የመረጃ ምንጮች



የፈተና ዕቅድ ዓይነቶች

አጠቃላይ የፈተና ዕቅድ ዝግጅት

- አጠቃላይ የትምህርት ይዘቶች የየምዕራፉ ክፍለ ጊዜ ከየምእራፉ የሚዘጋጁ የጥቄዎች ብዛት የሚያሳይ ነው ሆኖ ዝርዝር ሁኔታዎችን አያሳይም
- ጠቀሜታው አጠቃላይ ሪፖርት ለማድረግ ወይም ለመምህሩ የሚቀጥሉትን ዕቅዶች ለመስራት እንደ መነሻ በመሆን ከማገልገል የበለጠ ጠቀሜታ የለውም።ከዚህ ዕቅድ ተነስቶ ትክክለኛ ፈተና ለማዘጋጀት እጅግ አስቸጋሪነት አለው

ዐብይ የትምህርት ይዘቶች	ይዘቶችን ለማስተማር የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት	የፈተና ጥቄ ብዛት ከተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት አንፃር	የጥያቄ ብዛት በመቶኛ
ክፍለ ትምህርት አንድ ጠፈርና ዓለም	37 ክ/ጊዜ	20	50
ክፍለ ትምህርት ሁለት የኣለም ህዝብ ባህሎችና ቋንቋዎች	18 ክ/ጊዜ	9	22.5
ክፍለ ትምህርት ሶስት የዓለም ታላላቅ ዕሳቤዎች	21 ክ/ጊዜ	11	27.5
ድምር	76 ክ/ጊዜ4	40	100

ከዚህ አጠቃላይ የፈተና ዕቅድ በመነሳት የፈተና ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት አይቻልም።ምክንያቱም ይህ ዕቅድ ከእያንዳንዱ ምዕራፍ ምን ያህል ጥያቄ መዘጋጀት እንዳለበት ከመጠቆም በቀር እያንዳንዱ ጥያቄ ከየትኛው የትምህርት ርዕስ ወይም ከየትኛው ዝርዝር ዓላማ እንደሚዘጋጅ አያመለክትም ።የፈተናው ዓይነት እውነት ሃሰት ይሁን የምርጫ ጥያቄ ይሁን ወዘተ አያመልክትም

- አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች ዋናና ንዑሳን ይዘቶች የክፍለ ጊዜ መጠን ከዋናና ከንዑሳን ይዘቶች አኳያ የጥያቄ ብዛት ከተመደበው የክፍለ ጊዜ ብዛት አኳያና ከንዑሳን ይዘቶች አንጻር የሚያሳይ ነው

የፈተና ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ትኩረት መደረግ ያለበት በትምህርት ዓላማዎች ላይ እንጂ በይዘት ላይ መሆን የለበትም

ጥያቄ ለመቅረፅ የሚያግዙ ዝርዝር የትምህርት ዓላማዎች ከእያንዳንዱ አጠቃላይ ዓላማና አብይ ይዘት አኳያ ይቀረፃሉ።ከዚህም በተጨማሪ የክፍለ ጊዜ ድል ድልና የጥያቄ ብዛት ከበፊቱ በተሻለ ከንዑሳን ይዘቶች አንፃር ዘርዘር ብለው ሊቀመጡ ይገባል።ይሁን እንጂ ይህም በራሱ የመጨረሻ ሊሆን አይችልም ምክንያቱም በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሁለት ዓይነት መረጃዎች ይጎሉታል።ይሄውም የሚዘጋጁት የፈተና ጥያቄዎች ከሚመዘኑ ተማሪዎች የባህሪ ለውጥና ከፈተና ዓነቶች አንጻር በመካከለኛ የፈተና ዕቅድ ውስጥ በዝርዝር ስለማይታይ ነው

አጠቃላይ ትምህርት ዓላማዎች	ዝርዝር የትምህርት ኣላማዎች (የፈተና ጥያቄዎች ለማዘጋጀት በሚረዳ መልኩ የተቀረፀ)	ይዘቶች		የጥያቄ
ክፍለ ትምህርት አንድ				
ክፍለ ትምህርት ሁለት				
ክፍለ ትምህርት ሶስት				
		ድመር		

አጠቃላይ ትምህርት ዓላማዎች	ዝርዝር የትምህርት ኣላማዎች (የፈተና ጥያቄዎች ለማዘጋጀት በሚረዳ መልኩ የተቀረፀ)	ይዘቶች	ብዛት	የጥያቄ ብዛ
ክፍለ ትምህርት አንድ ጠፈርና ዓለም			37	20
የጠፈር አካላት ምንነት ያውቃሉ	1. የጠፈርን መጠን ይለያሉ 2. የጠፈርን ልዩ ልዩ አካላት ይዘረዝራሉ	1. የጠፈር አካላት	4	2
የመሬትን ቅርፅ መጠን እንቅስቃሴዎችንና የሚያስከትሏቸውን ክስተቶች ይገነዘባሉ	1. መሬት ክብ ቅርጽ እንዳላት ያብራራሉ 2. የመሬት ዋና ዋና የእንቅስቃሴ ዓነቶችን ይገልፃሉ 3. የመሬት አዟዟር የሚስከትላቸውን ውጤቶች ዘረዝራሉ 4. ሶስቱን ውጫዊ የመሬት ክፍሎች ይለያሉ	1.2 መሬት	12	7
የሉልና የካርታ ምንነትንና አጠቃቀምን ያውቃሉ	1. የሉልና ካርታ ምንነትን በተማሩት መሰረት ይናገራሉ 2. የሉልና ካርታን ተመሳሳነትና ልዩነት ይለያሉ	1.3 ሉልና ካርታ	5	2
የዓለም ዋና ዋና የተፈጥሮ ሃብት ክምችትን ይረዳሉ	1. የተፈጥሮ ሃብት ክምችትን ሥርጭትን ጥቅምን ይተነትናሉ 2. የተፈጥሮ ሃብት ክምችት ከህዝብ ዕድገት ጋር ያላቸውን ዝምድና ይለያሉ	1.4 የዓለም ተፈጥሮ ሃብት	9	5
1. የዓለም ህዝብ ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ እንደሚሄድ ይገነዘባሉ 2. የሕዝብ ሥርጭትንና ዕድገትን የሚቆጣጠሩ አጠቃላይ ሁኔታዎችን ይረዳሉ	1. በታዳጊ እና በበለፀጉ ሃገሮች መካከል ያለውን የህዝብ ቁጥር ዕድገትን ያነጻፅራሉ 2. የዓለም ህዝብ እድገትንና ስርጭት ስለሚቆጣጠሩ ሁኔታዎች ያብራራሉ	1.5 የዓለም ህዝብ	7	4
ክፍለ ትምህርት ሁለት የዓለም ሕዝቦች ባህሎችና ቋንቋዎች			18	9
2.1 የሰው ዘር አመጣጥና አሰፋፈርን ይገነዘባሉ	1. የሰው ዘር አመጣጥ የተጠናባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ 2. የሰው ልጅ ዝርያ መነሻውንና የዕድገት ደረጃዎቹን ይዘረዝራሉ	2.1 የሰው ልጅ አመጣጥና የዘር ግንድ	4	2
2.2 የባህል ምንነትን አመጣጥና ዕድገት ይገነዘባሉ	1. ባህል ሲባል ምን ምን እንደሚያካትት ይተነትናል 2. ከዘመናት አኳያ የባህል ዓይነቶችን ያነፃፅራሉ 3. ጎጂና ጠቃሚ ባህሎችን ይለያሉ	2.2 የኣለም ህዝብ ባህሎች	7	3
3. በዓለም የሚገኙ ዋና ዋና ቋንቋዎችን ያቃሉ	1. የቋንቋን ትርጉም ይገልፃሉ 2. የቋንቋን ጥቅሞች ይዘረዝራሉ 3. የዓለም ዋና ዋና ቋንቋዎችን ይዘረዝራሉ	2.3 የዓለም ዋና ዋና ቋንቋዎች	3	2
2.4 ከቆዳ ቀለም አንፃር የዓለም ህዝብ ሥርጭትንና ብዛትን ይገነዘባሉ	ልዩ ልዩ ቀለም ያላቸው የዓለም ህዝቦች የት እንደሚኖሩ ይጠቅሳሉ ከቆዳ ቀለም አኳያ የዓለም ዋና ዋና ህዝቦች ብዛት ያነፃፅራሉ	2.4 የኣለም ህዝብ ሥርጭትና ብዛት ከቆዳ ቀለም አንጻር	4	2
ክፍለ ትምህርት ሶስት የኣለም ታላላቅ ዕሳቤዎች			21	11
3.1	**.....**		2	1
.....	**.....**	**.....**		
.....	**.....**	**.....**		
3.8	**.....**	**.....**	4.	2

ዝርዝር ፈተና ዕቅድ ዝግጅት

ፈተና የሚዘጋጅባቸው ምዕራፎችና ንዑሳን ርዕሶች የክፍለ ጊዜ ብዛት የጥያቄ ብዛት እያንዳንዱ ጥያቄ ከሚመዝኑት የተማሪው ባህሪ ለውጥ ደረጃ አንጻር የሚያሳይ ነው



ዝርዝር የፈተና ዕቅድ ከፈተና ዓይነቶች አንጻር

የምዕራፍ ተ.ቁ	ዝርዝር ይዘቶች	የክፍለ ጊዜ ብዛት	የጥያቄ ብዛት	የሚመዘኑ ባህሪያት				
				ማስታወስ	መገንዘብ	በተግባር ማሳየት	ድምር	በመቶኛ
1.1		4						
1.2		12						
1.3		5						
1.4		9						
1.5		7						
2.1		4						
2.2		7						
2.3		3						
2.4		4						
3.1		2						
3.2		2						
3.3		3						
3.4		2						
3.5		4						
3.6		2						
3.7		2						
3.8		4						
	ድምር	76	40					
	በመቶኛ							

የምዕራፍ ተ.ቁ	ዝርዝር ይዘቶች	የክፍለ ጊዜ ብዘት	የጥያቄ ብዛት	የፈተና ዓይነቶች						
				እውነት /ሃሰት	አዛምድ	ባዶ ቦታ ሙላ	ምርጫ	በተግባር አሳይ	ድምር	በመቶኛ
1.1		4								
1.2		12								
1.3		5								
1.4		9								
1.5		7								
2.1		4								
2.2		7								
2.3		3								
2.4		4								
3.1		2								
3.2		2								
3.3		3								
3.4		2								
3.5		4								
3.6		2								
3.7		2								
3.8		4								
	ድምር	76	40							
	በመቶኛ									